አደፍርስ - የብዕር ጠብታ

የመጽሐፉ ርዕስ - "አደፍርስ"

ደራሲ - ዳኛቸው ወርቁ

የታተመበት ዘመን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም

ቅንጣቢ ዳሰሳ - በሔኖክ ሥጦታው

http://henoksitotaw.blogspot.com/

ደራሲና ጋዜጠኛ ዘነበ ወላ ባስነበበን መዝገበ-ስብሐት "ማስታወሻ" መጽሐፍ ላይ ጋሼ ስብሐትን እንዲህ ሲል ጠየቀው፥- "በአንተ የወጣትነት ጊዜ በአማርኛ ሃሳብን መግለፅ አይቻልም ብላችሁ አንተም ሆንክ ጓደኞችህ በእንግሊዝኛ መጻፍ የወሰናችሁበት ወቅት እንደነበረ ይነገራል። በኋላ ደግሞ ወደ አማርኛው ተመልሰህ ድንቅ ጸሐፊ ወጣህ። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ብትገልፅልኝ?"

ስብሐት ገብረእግዚአብሔር፦ "በወጣትነቴ አማርኛ በምፈልገው መልኩ ሀሳብን መግለፅ አያስችልም የሚል እምነት ነበረኝ። በዚህም ላይ ያስተማሩን እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች መሆናቸውን አትርሣ። እኛ አናውቅም እንጂ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ወጣቱን ትውልድ በቅኝ አገዛዝ ጥበባቸው ይዘውናል። በኋላ ዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስን" ጻፈ። እኔ ሳነበው በአማርኛ መጻፍ እንደሚቻል ገባኝ። ስለዚህ በእንግሊዝኛ የመጻፍ ሀሳቤን ተውኩት። በወቅቱ አስታውሳለሁ "ሌቱም አይነጋልኝን" በእንግሊዘኛ መጻፍ ጀምሬው ነበር። . . ."

ማስታወሻ (ስብሐት ገብረእግዚአብሔር) ከዘነበ ወላ ፤ 1993 ዓ.ም ታተመ፤ ገጽ 238

****** ****** ****** *****

ጥቂት ስለ ዳኛቸው ወርቁ



ዳኛቸው ወርቁ «አደፍርስ» (፲፱፻፷፪ ዓ.ም.) በተሰኘ ልብ ወለድ ድርሰቱ. . . .ጭብጦች እና የተራቀቀ የአጻጻፍ ስልቱ የአማርኛን ዘመናዊ ልብ ወለድ ወደ ድንቅ ከፍ ካለ እርከን ያወጣ፥ «እምቧ በሉ ሰዎች» በሚለው የግጥም መድብሉ (፲፱፻፷፯ ዓ.ም.) ውስጥ በተካተቱ ግጥሞቹ ስለሀገሩ ልማትና ዕድገት ተቆርቋሪነቱን

የገለጠ ዕውቅ የሥነ ጽሑፍ ምሁር፥ ሐያሲና ተርጓሚ የነበረ ሲሆን በልሳነ እንግልጣር (እንግሊዝኛ) በመጻፍም «The Thirteenth Sun» የኢትዮጵያን ሥነ ጽሑፍ በዓለም አቀፉ መድረክ ካስተዋወቁ በጣት ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ጸሐፍት አንዱ ነበር።" ይለዋል የአማርኛው ዊኪ ፔዲያ።ሲቀጥልም፥ -

"የፊውዳል ኢትዮጵያን ሶሲዮሎጂና የታሪክ ጥራዞች ከማንበብ፥ «አደፍርስ» ድርሰቱን ማንበብ ይቀላል' የተባለለት ዳኛቸው ወርቁ የካቲት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ በይፋትና ጥሙጋ በደብረ ሲናከተማ አቅራቢያ ከአቶ ወርቁ በዛብህና ከወይዘሮ አሰገደች ሀብተወልድ ተወለደ። ከቤተ ሰቡ አምሥት ልጆች ዳኛቸው በኩር ነበር።...

የዛሬዎቹን ወጣት ኢትዮጵያውያን በጥበቡ ዘርፍ የሚታደጉ የሥነ ጽሑፍ ጥበብ መመሪያ፣ የአማርኛ ፊሊጦች መጽሐፍት ያሳተመ ምሁር ሲሆን አንድም ለሀገሪቱ ቋንቋ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያላቸውን «የማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገበ ቃላት» እና «የሳይንስና ቴክኖሎጂ መዝገበ ቃላት» የመሳሰሉ ጥልቅ እና ምጡቅ ሥራዎች ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ምሁራዊ ግዴታውን የተወጣ ኢትዮጵያዊ ነበር።

"የሀገሩን እምነትና ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅ፥ ለሥራ ነገን የማያውቅ፥ ለውጥ ፈላጊ፥ አገር ወዳድ፥ ስለሀገር ኋላ ቀርነት ሁሌ የሚቆረቆር ፥ ማኅብደድና ማቆሻበድ የማይወድ፥ ፊት ለፊት ተናጋሪ ባጠቃላይ በ«አደፍርስ» ልብ ወለድ ድርሰቱ ጠጣርና ምጡቅ ሐሳቦች በድንቅና ውብ የአጻጻፍ ስልት፥ ልዩ በሆነ የቋንቋ ኃይል የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ልዕልና ያሳየ - ዳኛቸው ወርቁ - በዚሁ ድርሰቱ የፊጠራ መጽሐፍ የሚነበብ ብቻ ሳይሆን ተደጋግሞ የሚነበብና የሚያወያይ መሆኑን - አዲስ ባህል የተከለ ብርቅ የጥበብ ሰው ነበር። . . ." በማለት የአማርኛው ዊኪ ፔዲያ መዝገበ - ሕይወቱን ያስነብበናል።

****** ****** ****** *****

ስለ አደፍርስ ልብ ወለድ ድርሰት ሐምሌ (፲፱፻፺፫ ዓ.ም.) "አዲስ ርዕዮት" ጋዜጣ ላይ በጥበብ አምድ ስር "አደፍርስ - የብዕር ጠብታ" በሚል ርእስ ቁንጽል ምልከታዬን እንዲህ አስነብቤ ነበር፥ -

በ (፲፱፻፵፰ ዓ.ም.) ከታተሙ ሁለት የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ - ጽሑፍ ፊር ቀዳጅ መጻህፍት ውስጥ አንዱ በዳኛቸው ወርቁ የተደረሰው አደፍርስ ሲሆን የድርሰቱን ዘመናዊ አቀራረብ ባልተረዱ አንቢያን ተቀባይነት አጥቶ እንደነበር ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው። በዚሁ ዓመት የታተመው ሌላው መጽሐፍ በበዓሉ ግርማ የተደረሰው "ከአድማስ ባሻገር" ነበር።

የወቅቱ ማሕበረሰብ በአደፍርስ ውስጥ ነፍስ ዘርተው ሲንቀሳቀሱ ይታሉ። ወግ፣ ባሕል፣ እምነት፣ ሥነ - ልቦና . . .አብሯቸው ይተማል። ምዕራፉት የየራሳቸውን የብዕር ጠብታ እየፈነጠቁ ይጓዛሉ። ሕይወት ለአደፍርስ፣ ሕይወት በአደፍርስ ይገለጻል።

ርዕሳችን የሆነው "አደፍርስ" በደራሲው ዳኛቸው ወርቁ አቀማመጥ ፣ "ጠይም ነው፣ ፊተ ሰልካካ።ቀጭን ነው፣ ቁመተ ለግላጋ።ሃያ አራተኛ ዓመቱን ይዟል - ከተወለደ።" ለአለባበሱም ሆነ ለላይ ውበቱ ጭንቅ የለው። ባሰኘው መንገድ ይጓዛል። "ሞትና ሕይወት፣ ድንቁርናና እውቀት መፈራት የለባቸውም" የሚል ፈሊጥ አለው። "ልቡሰ ጥላ" የሚለው ቃልም ለአደፍርስ የእውነት መገለጫነት ትልቅ ቦታ አለው።

"ልቡሰ ጥላ" ለአደፍርስ፣ መያዣ መጨበጫ የሌለው ምስቅልቅል ሁኔታ ነው። ከአዕምሮ ክፍሎች በአነስተኛው ውስጥ የሚገኝ ልዩልዩ ነገሮች ማየትና ማውጠንጠን ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የሚጠራቀም ነው - ይላል።ልቡሰጥላ በተለያዩ መንገዶች የሚገኝ ውስጣዊ ግፊት ነው። የመፈለግ ፍላጎት። ከየዕለታዊ ተግባሮቻችን ከሚጠቅመንም ሆነ ከማይጠቅመን፣ ከመልካሙም ሆነ ከመጥፎው ፣ ለዓይናችን ከሚያስደስተንም ሆነ ከሚያስጠላን ሁሉ ወደ አዕምሯችን እየገባ የሚጠራቀም "ስሜት" ነው። እነግድህ ለአደፍርስ ልቡሰጥላ ይህን ትርጓሜ ይይዛል።



ገጾች ሲገለጡ ፣ገፀ - ባህርያት ሲላወሱ፤ ሰዓሊው ክብረትን እናገኘዋለን።ልዩ ባህርይን ተላብሷል። በሰዎችም ሆነ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚመለከተው ውበትን ነው። የላይን ሳይሆን የውስጥን ገፅታ።ደራሲው ዳኛቸው ወርቁ፣ ክብረት በገዛ አንደበቱ ማንነቱን ያሳየናል። ገጸባህርያት በንግግራቸው ይለያሉ ። ንግግራቸው ድርጊታቸውን ይገልፀዋል። ክብረትም ይናገራል፤ ንግግሩ ሙያውን ያሳይበታል። አደፍርስ የክብረትን አስተሳሰብ ይጋራል። "ሰዓሊ

ተግባሩ ውስጣዊውን ንቅናቄ አፍልቆ ማሳየት ነው መሆን ያለበት" ይለዋል። እርግጥ ሰዓሊው ክብረት ወጣትን ሳይሆን ወጣትነትን ለመሳል በሚያደርገው ጉዞ የስሜቱ ተጋሪ አደፍርስ ብቻ ነው። እናም የዘወትር እውነታውን ሳይሆን ውስጣዊውን ሰብእና ሊደርስበት የሚሻው ሰዓሊው ክብረት አጋዥ አላጣም።(በተቃራኒው በማሕበረሰቡ ልምድና ስርአት ጋር ለሚጋጨው አደፍርስ የደጋፊነት ሚና ይስተዋልበታል) ።

ወ/ሮ አሰጋሽ በወቅቱ በነበረው የፊውዳል ስርአትን ወክለው የተቀረፁ የቀለም ጠብታ ውጤት ናቸው።ህሊናዊ ገጽታቸውን ዘልቀን ለመመልከት የሚያስችሉ ድርጊቶች የመጽሐፉ አብይ አላማ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለአደፍርስ እንዲህ ሲሉት እንሰማለን፥ -

"ከሰውም ሰው አለው፤ "ከእንጨት መርጦ ለታቦት፤ ከሰው መርጦ ለሹመት" ሲባል አልሰማህም የኔ ልጅ . . .አሁን ለምሳሌ አሽከሮቼን ገና ለገና በዝጌር አምሳል ተፈጥረዋል ብዬ ከኔ ጋር እኩል ናቸው ልል ነው? የለም የኔ ልጅ፣ ዙሪያውንም፣ አካባቢውንም እያዩ ነው ጨዋታ . . ." (ገፅ 101) ይሉታል። የወ/ሮ አሰጋሽን ሰብእና ለመረዳት ጥቂት ንግግራቸውን መስማት በቂ ነው። እዚህ ላይ ደራሲው ገፀባህሪያቱን በንግግራቸው እንዲለዩ የማድረግ ጥበቡን በመጽሐፉ ላይ በሰፊው ተጠቅሞበታል።

ለወ/ሮ አሰጋሽ የእኩልነት ጥያቄ ቦታ የለውም።ሰው በፈጣሪ አምሳል መፈጠሩን ያምናሉ፤ መተቃራኒው ደግሞ ጌታና ሎሌ መኖሩን ያስረግጣሉ። "የአካባቢ ሕግ" ተከታይ ናቸውና። የአደፍርስ አመለካከት ለእርሳቸው የ"አይነጥላ" ውጤት ነው። ለዚህም "አባዜ" መፍትሄ ስራይ "የድንገተኛ" ቅጠል ብጠሳ ይጓዛሉ። "ድንገተኛ ይፈውሰው ይሆን?"ን እያሰላሰሉ።

አደፍርስ የዘመን አሻራ ነው። ልክ እንደሱው ሁሉ ሌሎች ደራሲያንም በቀረጹት ገፀባህሪያት የዘመኑን አሻራ አትመው አኑረውልናል። "ፍቅር እስከ መቃብር" በጉዱ ካሳ፤ "አደፍርስ" - በአደፍርስ፣ "ከአድማስ ባሻገር" - በኃይለማርያም፤ "ሀዲስ" - በሀዲስ። በበዓሉ ግርማ የተደረሰው "ሀዲስ" ልብወለድ መጽሐፍ፣ ከወግ እና ባህል ጋር የሚጣረሰው አደፍርስ ጋር ተወራራሽ ባህርይ ይስተዋልበታል። አደፍርስ እና ሀዲስ የትላንቱን፣ የዛሬውንና የነገን ድርጊቶች አንግበው ሲጓዙ ይታያል።በተመሳሳይ መልኩ የፍቅር እስከመቃብሩ ገፀባህርይ ካሳ ዳምጤ(ጉዱ ካሳ)፣ በአደፍርስ ምስለ-ባህርይ ውስጥ ይታያል።ከአድማስ ባሻገሩ ኃይለማርያም የአደፍርስን ሰብእና ሲገለጥ የሚታይ ሌላ ባህርይ ነው። /ተወራራሽ ባህሪያትን በሌላ ርዕስ በሰፊው እመለስበታለሁ/።

አደፍርስ የብዕር ጠብታ ነው። ከልማድ እና ስርአት ጋር አንገት ለአንገት እንደተናነቀው ሁሉ፣ ከእምነት ጋር ግብግብ ገጥሟል፤ "ለሠይጣን መስዋእት የታረደን በግ የበላ ሰው

ይቀሰፋል" የሚል እሳቤ ተብትቦ በያዘው ማህበረሰብ ውስጥ ህብረ-ጥምሮሽ ጎልብቶ እውነታው ፈጥጦ ሲወጣ፤ "እንቢ በል አንተ ሰው!" እያለ በሽለላ አስተጋብቷል።

አደፍርስ የብዕር ጠብታነው። የጥበብ *መታያ* - የእውነት *መገለጫ* ነው። ድብቅ ሰብእና የለውም። የገፀ-ባህሪው ውስጠ ምስል የግልፅነት የተከተለ ነው። የአገራችን ደራሲያን ለዋና ገፀባህሪይ ነግነት ለመስጠት የሚጠቀሙበት ተመሳሳይ የአሳሳል ስልት በአደፍርስ ላይ መስተወሉን ልብ ይለዋል።

"ቀልድ ጨዋታ የማላዘወትር፣ የተሰማኝን ሃሳብ ያስቀይማል አያስቀይምም ብዬ ሳላስብ ቀጥታ መግለፅ የምወድ..." ገፅ129 እያለ እራሱን የገልጸዋል። ከደራሲው አንባር ስለ አደፍርስ ግልፅ ባህርይ የነገረናል፤ "የማይቦዝን ፣ ስለውጤቱም እምብዛም የማያስብ፣ እንደልቡ የሚናገር፤ ተቃዋሚዎቹም ከራስ ፀጉሩ የበዙ ናቸው..."

ዳኛቸው ወርቁ ለአደፍርስ እንደልቡ የመናገር ነግነትን በመስጠት፣ የራሱን ነግነት እንዳወጀ እናስተውላለን። እውነታውም ይህ ነበር። የወቅቱን ስርአት፣ ስርአቱ ለዘመናት የፈጠረውን ተፅዕኖ፣ ጭቆና እና ብዝበዛ ብሎም አጉል ልማዶችን በአደፍርስ አማከኝነት አውግዟል። በደራሲው ውስጥ አደፍርስ አለ፤ በአደፍርስ ውስጠም ደራሲው ።

መጽሐፉ፣ በተማረው እና ባልተማረው ማህበረሰብ *መሀል* ለውን ለውጥ ያሳያል። ስለ*መሀይ*ምነት *መጥፋት* ያትታል። አደፍርስ ለኢትዮጵያ ያለውን ብሩህ ተስፋ ትምህርትን አስታኮ ይናገራል። *መዕራፍ* 26 ለዚህ ዋቢ የሚሆን ነው። የምዕራፉ ውይይት አደፍርስ በመጨረሻዎቹ ምዕራፍ ለያዘው *ሥራ መጠቆሚያ*ም ጭምር ሆኗል።

"ሀዲስ" እና "አደፍርስ"

አደፍርስ በዓሉ ግርማ የደረሰው "ሀዲስ" ረጅም ልብ ወለድ ዋና ገፀ ባህርይ ሀዲስ ላይም የባህርይ ተፅዕኖ ያሳደረ ይመስላል። የሀዲስ እና አደፍርስ እንቅስቃሴ የወቅቱ *መንፈስ* ታትሞባቸዋል። ሀዲስ *መስቀል መሳለም* ይሸሻል፤ አባቱ ግን ቄስ ናቸው። አደፍርስ ፀበል ይሸሻል፤ የወጣበት ማህበረሰብ ግን የፀበልን ፈዋሽነት አጥብቀው ያምናሉ። /ደራሲው የአደፍርስ ጤንነት ተደራሲው እንዲጠራጠር ፣ ሽፋን የመስጠት ዘንባሌን ለመፍጠር የሞከረበት ብልሃት ነው/ ። ሀዲስ እምነቱ "ሕይወት" እንደሆነ ይናገራል። የሚያምንበት ህይማኖት እንደሌለ አስረግጦ። ለአደፍርስ እምነት ማለት "እውነት" ነው። አሁንም ሀዲስ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ ኢደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚለውን ጥቅስ አይቀበለውም። አደፍርስም በገፅ 101 ላይ " ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የሚለውን ጥቅስ አጥብቆ ሲቃወም እናያለን።

ሀዲስ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች የከብት ጭራ እየተከተሉ ሲቀሩ ዝም ማለትን አይሻም። በአንፃሩ ትምህርት ቤት ለማሠራት ደፋ ቀና ይላል። አደፍርስም በገፅ 165 ላይ በእረኝነት ሕይወት የከብት ጭራ ተከትሎ ትውልድ እንዳይቀር መስኖጌ /የከብት ማቆሚያ/ መሠራት እንዳለበትና እረኛው እንዲማር የሚደረግበትን ብልሃት ያሰላስላል። የበዓሉ ግርማ "ሀዲስ" እና የዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ" አንድ የሚያደርጋቸው አብይ አላማ አለ። እሱም ለውጥ ! ነው።

የሁለት ባህርያት አንድነት፣ የሁለት መጻሕፍት የጭብጥ ተመሳሳይነት እንዳለ ሆኖ ቅርጽ ላይ ግን ከፍተኛ ልዩነት ፈጥረዋል። በዓሉ ግርማ "የህሊና ደውል"/1966ዓ.ም/ በሚል ስያሜ ያስነበበንን መጽሐፍ፣ የይዘት እና ቅርፅ እድሳት ተደርጎለት በ1975ዓ.ም "ሀዲስ" ተብሎ መታተሙ ይታወቃል።

በሀዲስ እና አደፍርስ ውስጥ ያሉ የአላማ ተመሳሳይነትን እንመልከት።

ሀዲስ "የድንቁርና ዛፍ" የሚለው የአምልኮ ዛፍ በሀዲስ ረጅም ልብ ወለድ መጽሐፍ ውስጥ ገዝፎ ይታያል። ለውጥ ፈላጊው ሀዲስ "ይህ ዛፍ መፈንዳት አለበት !" ብሎ ሲወስን ዛፉ የበቀለበት ቦታ የእውቀት ቤት እንዳይሠራ እንቅፋት ሆኖበት ነው። ዛፉ ተምሳሌት ነው። ታሪክ ሆኖ የቀረው ጥንታዊ እውቀታችን ላይ የበቀለ ዛፍ። ለዘመናት ሥሩን ሰዶ የዘለቀ ዛፍ። የሚፈራ፣ የሚመለክ ዛፍ። ዘሩን ከሰለሞናዊ የዘር ግንድ የሳበው ዛፍ ከንጉሣዊ አገዛዝ ሥርአት ጋር ያለውን ተዘዋዋሪ መልእክት ያስተውሏል። ይህ ዛፍ ካልወደቀ እውቀት አይኖርም።

የወቅቱ ስርአት ፣ ወግ፣ ባህል እና አስተሳሰብ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ብለው በአንድነት እንደቆሙ ታናሽ እና ታላቅ ወንድማማቾች ይመሰላሉ። አደፍርስ እና ሀዲስ።

የ"እጅ መንሻ" ስነስርአት አደፍርስ በፍፁም አያምንም። የመረረ ተቃውሞውንም አሰምቷል። "ልማድ ልተውህ ቢሉት የት ይተዋል...?" ከሚሉት ወ/ሮ አሠጋሽ ጋር ይጋጫል። በአስተሳሰብ። ወ/ሮ አሸጋሽ እግራቸውን የሚስምላቸው ሰው ከሌለ ሕይወት መጓዟን እንዳቆመች የሚደመድሙ ናቸው። አደፍርስ መቅረት አለበት የሚለውን "ወግ" ከቁብም አይቆጥሩ። ይበልጥ ግን ያጠናክሩታል፤ በተለይ ስለራሳቸው ክብር የእግር መሳም ጠቀሜታ ሲናገሩ፥-

"... እንደ እህል እና ውሃ አስፈላጊ ነው። ያለእሱ ለመኖር አይችል ህዝቡ..." ገፅ 208

ለክብሩ ከፍተኛ ቦታ ይሰጥ የነበረው ክፍል በወ/ሮ አሠጋሽ በኩል ይታያል።

መጽሐፉ ጥሉቅ ምጡቅ መልእክትን አጭቆ ይዟል። ምዕራፉት በተቆጠሩ ቁጥር ይበልጥ ውበት ይረጭበታል። ጠጣር ቋንቋዎቹ፣ የገፀ ባህርይ አሳሳሉና የመቼት አገላለፁ መለያዎቹ ናቸው። ለአላማው ስኬት ፣ ለአላማው ፅናት እንባ የማይሸረሽረው አደፍርስ ለቆመለት አላማ ውልፍት አይልም። እናም አደፍርስ ብዙ ነው፣ ግን አንድ። አደፍርስ አንድ ነው፤ ግን ብዙ - የብዕር ጠብታ።

አበቃሁ

ሄኖክ ስጦታው

http://henoksitotaw.blogspot.com/